# የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ፍርድ ቤቶች
## የዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶችን ችሎት በርቀት መከታተያ ጣቢያዎች (ሪሞት ሂሪንግ ሳይትስ) ለመጠቀም የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮች

በተመደበላቸው በርቀት የሚካሄዱ ችሎቶች ለመሳተፍ የኮምፒውተር መሳሪያዎች ወይም እቤት ውስጥ የኢንተርኔት አገልግሎት ለሌላቸው ግለሰቦች ጥቅም የሚውሉ ዲ.ሲ. ፍርድ ቤቶች በከተማው ማህበረሰብ የተለያየዩ አከባቢዎች **ችሎት በርቀት መከታተያ ጣቢያዎች (ሪሞት ሂሪንግ ሳይትስ)** አዘጋጅቷል። ፍርድ ቤቶቹ ፍትህ ለሁሉም ተደራሽነት ለማሳደግ ቁርጠኛ ናቸው።

**ከሰኞ - አርብ፣ 8:30 ኤ.ኤም. - 4:00 ፒ.ኤም.** የሚሰሩ በመላው ማህበረሰቡ አምስት የርቀት መከታተያ ጣቢያዎች አሉ።

**በርቀት መከታተያ ቦታዎቹ (ሪሞት ሳይት ሎኬሽንስ) የሚከተሉት ናቸው፡**

**የርቀት ጣቢያ (ሪሞት ሳይት) - 1**
ሚዛናዊና አዳሽ ፍትህ ማእከል (ባላንስ ኤንድ ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ሰንተር)
1215 South Capitol Street, SW
Washington, DC 20003

**የርቀት ጣቢያ (ሪሞት ሳይት) - 2**
ሚዛናዊና አዳሽ ፍትህ ማእከል (ባላንስ ኤንድ ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ሰንተር)
1110 V Street, SE
Washington, DC 20020



**የርቀት ጣቢያ (ሪሞት ሳይት) - 3**
ሚዛናዊና አዳሽ ፍትህ ማእከል (ባላንስ ኤንድ ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ሰንተር)
118 Q Street, NE
Washington, DC 20002

**የርቀት ጣቢያ (ሪሞት ሳይት)- 4**
ሚዛናዊና አዳሽ ፍትህ ማእከል (ባላንስ ኤንድ ሪስቶሬቲቭ ጀስቲስ ሰንተር)
920 Rhode Island Avenue, NE
Washington, DC 20018

**የርቀት ጣቢያ (ሪሞት ሳይት)- 5**
ሪቭስ ማእከል (ሪቭስ ሰንተር)
2000 14th Street, NW, 2nd Floor – Community Room
Washington, DC 20009

ለችሎትዎ በርቀት መከታተያ ቦታ መጠቀም የሚፈልጉ ከሆነ **ችሎትዎ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ24 ሰአታት አስቀድመው በርቀት መከታተያ የኮምፒውተር ጣቢያን ለማስያዝ (ሪዘርቭ ለማድረግ) 202-879-1900** ይደውሉ ወይም በ DCCourtsRemoteSites@dcsc.gov ኢ.መይል ያድርጉ። እንደነ አስተርጓሚ የመሳሰሉ ልዩ እርዳታዎች ለችሎትዎ የሚፈልጉ ከሆነ **ፍርድ ቤቱ ዝግጅቶች ያደርግ ዘንድ ከችሎትዎ ቢያንስ 24 ሰአታት አስቀድመው በ 202-879-1900** በመደወል ያሳውቁ።

***መርሐግብር ወደ ተያዘልዎ የርቀት መከታተያ ጣቢያ ሲመጡ የሚከተሉትን ነገሮች ይዘው ይምጡ***

1. **የመዝገብ ቁጥርዎና** ማናቸውም ፍርድ ቤቱ ለተቀጠረው የፍርድ ቤት ችሎትዎ የሚሆን የሰጥዎት **ሀይፐርሊንኮች።**
2. ኤግዚቢቶች፣ ደረሰኞ፣ ፎቶዎች፣ ውሎች፣ ወዘተ ያካተቱ ማናቸውም ለችሎቱ የሚያስፈልግዎ ሰነዶች (ማስረጃዎች)።
3. እንደነ እስክርቢቶና ወረቀት የመሳሰሉ ማስተወሻ መውሰጃ ቁሳቁሶች።
4. በርቀት መከታተያ ቦታዎች ለመግባት የፊት መሸፈኛ ማድረግ የግድ ይሆናል፣ የፊት መሸፈኛ የሌለዎት ከሆነ ይሰጥዎታል።

***በርቀት መከታተያ ጣቢያዎች ባሉባቸው ቦታዎች ደህንነት መጠበቂያ እርምጃዎች አሉ።**

**ለርቀት ተደራሽነት ኮምፒውተር ጣቢያ ለማስያዝ የሚሆን መገኛ መረጃ፡**

ቴሌፎን፡ **202-879-1900**
ኢ.መይል፡ DCCourtsRemoteSites@dcsc.gov